# የኢትዮጵያ ሕዝብ፣ አገር-ወዳድና ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች እና ኢሕአዴግ፤ <u>ከዚኽ ወዴት?</u>

*ከአያል ሰው ደሴ፤- የግል አስተያየት*

***<u>ክፍል አሥራ-ሁለት (ከክፍል አሥራ-አንድ የቀጠለ)፤-...</u>***

***<u>ሐ- ፬፤- የኢትዮጵያ ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች ኅብረት (ኢተፖድኅ) ፣ ፓሪስ-ሁለት፤-</u>***

*ከዚኽ በላይ እንደ-ተጠቀሰው ደርግ ሲወገድ የሕዝባችን ምኞትና ጥባቆ ለዝንታለም ቀስፈው የያዙት የአምባገነን ሥርዓቶች አዙሪት እንዲያከትምና መሠረታዊ የሆኑና ሥር የሰደዱ ፖለቲካዊ፣ ማኅበራዊና ኤኮኖሚያዊ የወል ችግሮቻችን በሰከነ አገራዊ የእርቅና ሰላም ሂደት የሚፈቱበት መንገድ ይመቻች ይሆናል የሚል ነበር፡፡ ይሁንናም በወቅቱ ደርግን የተካው የሕወሓት/ኢሕአዴግ "የሽግግር" መንግሥት የተከተለው ሂደት የለውጡ አቅጣጫ ሕዝቡ በጉጉት በጠበቀው መልክ ሣይሆን የዴሞክራሲው መንገድ ፈር እየለቀቀ እንዲሄድና ሕዝባችንን ልዩነት ማስፋትን የግድ በሚያስከትል ጎሣን/ቋንቋን መሠረት ላደረገ ከፋፋይ መንግሥታዊ መዋቅር እያደላደለ፣ እራሱንም ወደ-አንድ ፓርቲ ፍጹም አምባገነን የአገዛዝ ሥርዓት እያመቻቸ መገኘቱ ግልጥ ነበር፡፡ ለዚያ አሳሳቢ ሁኔታም ምላሽ ለመስጠት ለለውጥ የቆሙ አገር-ወዳድና የዴሞክራሲ ኃይሎች ገና ከጅምሩ የሚያደርጉትን ጥረት በመቀጠል ትግላቸውን አስተባብረው የአገራችንንና የሕዝቧን አንድነት አስጠብቆ ከመንገድ የወጣውን ሂደት መልክ ለማስያዝ ይቻል ዘንድ ትልቅ ተስፋ የተጣለበትን የኢትዮጵያ የሰላምና የዴሞክራሲ አማራጭ ኃይሎች ምክር-ቤትን በአገር ውስጥ መመሥረታቸው ይታወቃል፡፡ ሆኖም ቀደም-ሲል በተጠቀሱት ምክንያቶች ኢሰዴአኃ በተቋቋመበት መንፈስ ተልዕኮውን መወጣት ወደማይችልበት ደረጃ መድረሱ ይበልጥ ግልጥ እየሆነና በአኳያው ሕወሓት/ኢሕአዴግ በምርጫ ስም እራሱን ለማጠናከር ጥድፊያ ላይ የነበረበት ወቅት ስለነበር፣ ጉዳዩ በጥብቅ ያሳሰባቸው ወገኖች የጋራ ትግሉ መልሶ መልክ እንዲይዝ መፍትኄ ከማፈላለግ ወደ-ኋላ አላሉም፡፡ በዚኽም መሠረት በግንባር-ቀደምትነት የአዲስ አበባውን አገር-አቀፍ የሰላምና የእርቅ ጉባዔ እንዲያዘጋጅ በፓሪስ-አንድ ስብሰባ ተሰይሞ ከነበረው አካል (ኮሚቴ) ውስጥ በተወሰኑት ወገኖች ጥረትና ግፊት የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ቅንጅት (ኢዴኃቅ)፣ የደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ ኅብረት (ደኢሕዴኅ)፣ የኢትዮጵያ መድኅን ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ (መድኅን)፣ የአፋር ዓብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ አንድነት ግንባር (አርዱፍ)፣ የትግራይ ዴሞክራሲያዊ ትብብር (ታንድ)፣ የትግራይ-ትግሪኝ ኢትዮጵያ (ቆየት ብሎ የኢትዮጵያውያን ለሶሻል ዴሞክራሲ) ተወካዮች አምስተርዳም (ሆላንድ) ላይ ሰኔ ሃያ እና ሃያ-አንድ ዘጠና ዓ/ም ባደረጉት ስብሰባ ጉዳዩን በጥልቀት መርምረው አጠቃላይ ሁኔታው አስቸኳይ የጋራ ምላሽን እንደሚጠይቅ በመስማማት ባለ ሰባት ነጥብ የውሳኔ አሳቦችን አስተላልፈዋል፡፡ ትግሉ የሁሉንም ለውጥ ፈላጊ ወገኖች በጋራ መቆምና ተቀባይነትና ተአማኒነት ያለው አማራጭ ለሕዝብ ማቅረብን፣ ለዚኽም ጠንካራና እርባና ያለው ማዕከል የሚሆን የጋራ ድርጅት መኖርን መጠየቁ ግንዛቤ የተወሰደበት በመሆኑ በአዲስ መልክ የኃይሎች መሰባሰብ እንዲኖርና ለተግባራዊነቱም አስቸኳይ እንቅስቃሴ ለማድረግ ወሰኑ፡፡*

*በውሳኔውም መሠረት ሁሉም በአገር-ውስጥም ሆነ ከአገር-ውጭ የሚገኙ በተቃዋሚው ጎራ የተሰለፉ ኃይሎች የሚሣተፉበት ጉባዔ በፓሪስ ከተማ ተጠራ፡፡ ይኽ በተለምዶ ፓሪስ-ሁለት በመባል የታወቀውና ከዓርብ መስከረም አንድ እስከ እሁድ መስከረም ሦስት ቀን ፲፱፻፺፩ ዓ/ም ለሦስት ቀኖች የተደረገ ጉባዔም ከአማራጭ ኃይሎች ትግል የተገኘውን ልምድ በቀና መንፈስ ገምግሞ፣ የጋራ ሕዝባዊ ትግሉን በአዲስ መንፈስና በአዲስ አደረጃጀት መልክ አስይዞ ለማስቀጠል ይቻል ዘንድ የኢትዮጵያ ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች ኅብረትን - ኢተፖድኅን መሠረቱ፡፡ በዚኽ ጉባዔ ላይ ከኦነግ በስተቀር ቀደም-ሲል በፓሪስ-አንድ ስብሰባ*

ላይ ተካፋይ የነበሩና ሌሎችም ተገኝተዋል፡፡ በጉባዔው ተሣታፊ የነበሩ ድርጅቶች፤ በኢትዮጵያ የሰላምና የዴሞክራሲ አማራጭ ኃይሎች ምክር-ቤት (ኢሰዴአኃ)፣ የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ቅንጅት (ኢዴኃቅ)፣ የደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ ኅብረት (ደኢሕዴኅ)፣ የኢትዮጵያ መድኅን ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ (መድኅን)፣ የአፋር ዓብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ አንድነት ግንባር (አርዱፍ)፣ የትግራይ ዴሞክራሲያዊ ትብብር (ታንድ)፣ የትግራይ-ትግሪኝ ኢትዮጵያውያን ለሶሻል ዴሞክራሲ፣ የኦሮሞ ብሔራዊ ኮንግረስ ነበሩ፡፡ የመላው አማራ ሕዝብ ድርጅት (መአሕድ) "የትጥቅ ትግል የሚያካሂዱ ኃይሎች ያሉበት ስብስብ ውስጥ መግባት ይቸግረኛል" የሚል ያልተጠበቀ ምክንያት በመስጠት የጉባዔው ተሣታፊ አልሆነም፡፡ *(ጉባዔው መዝጊያ ላይ በወቅቱ የአውሮጳ ፓርላማ የልማትና ትብብር ኮሚሽን ፕሬዝደንትና የፈረንሣይ የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ ሚሼል ሮካር ስብሰባው ኢተፖድኅን በማቋቋም በመጠናቀቁ የተሰማቸውን ደስታ በመግለጥና በኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እንዲኖር ድርጅቶችና የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚደርጉትን ጥረት በማበረታታት ንግግር አድርገዋል፡፡)*

ኢተፖድኅን ያቋቋመው ጉባዔ የተጠናቀቀው የድርጅቱ የተስማማባቸውን ዓላማዎች በተግባር ለመተርጎምና በውጭና በውስጥ የሚያደርገውን እንቅስቃሴ የሚያስተባብሩና ትግሉን የሚመሩ ኃላፊዎችን በመምረጥ ነበር፡፡ በዚሁም መሠረት ከኢዴኃቅ ዶ/ር ነገደ ጎበዜ ሊቀ-መንበር፣ ከታንድ አቶ (አሁን ዶ/ር) አረጋዊ በርኼ ምክትል ሊቀ-መንበር፣ ከመድኅን አቶ ማሞ ይሁኔ ዋና-ፀሐፊ እና ከደቡብ ኅብረት አቶ ክፍሌ ጥግነህ ምክትል ሊቀ-መንበር ሆነው በአገር-ውስጥ ለሚገደረው እንቅስቃሴ ኃላፊ እንዲሆኑ ተወሰነ፡፡

ወቅቱ በአንድ በኩል የኢሕአዴግ መሪዎች የ፲፱፻፺፪ን አገር-አቀፍ ምርጫ ዴሞክራሲ በእግሩ እንዲቆምና ሕዝብ የመብቱ ባለቤት እንዲሆን ሣይሆን አገዛዙ ሥር እንዲሰድና እንዲደላደል በሚያስችል ሁኔታ እንዲጠናቀቅ ከጅምሩ ወደ-ጠርዝ ተገፍቶ የቆየውና አንድነቱን አጠናክሮ መገኘት ያዳገተው እውነተኛ ተቃዋሚ ክፍልም ለሕዝብ አማራጭ ሆኖ እንዳይቀርብና ጨርሶም እንዲበታተንና ዳር እንዲወጣ ጥረት የሚያደርጉበትና፣ በሌላ በኩል እነሱ ባዘጋጁት፣ ሙሉ-በሙሉ በሚቆጣጠሩትና በብቸኝነት በሚመሩት ምርጫ ብቻቸውን ከራሣቸው ጋር ተወዳድረው ብቻቸውን "አቸነፍን" ማለቱ በተለይ በባዕዳን እርዳታ ሰጭዎቻቸውና ሞግዚቶቻቸው ዘንድ ተቀባይነት እንዳይቀንስባቸውና ከዚያም ጋር ተያይዞ የሚመጣውና ለኅልውናቸው መቀጠል አስፈላጊ የሆነው ሁሉን-አቀፍ እርዳታቸው እንዳይጎድልባቸው በማስላት፤ ተቃዋሚው ተሣታፊ ሆኗል እንዲባልና "ተወዳድረው በሕዝብ አብላጫ ድምፅና ይሁንታ" ሥልጣን እንደያዙ ለማስመሰል በሕጋዊ ሽፋን-ሰጭነት የሚያገለግሉ አንዳንድ ድርጅቶችን በድለላና በማስፈራራት ጭምር ከጎናቸው ለማሰለፍ ደፋ-ቀና የሚሉበት፣ በሌላ በኩል በሽዓብያ ዕብሪተኛ መሪዎች አርቆ-ያላዩ አጉል ጀብደኝነት ምክንያት በተጫረ ወረራ በአገሪቱ አጠቃላይ ውጥረት የተፈጠረበትና ገዥውን ፓርቲ ኢሕአዴግንም ሆነ ተቃዋሚውን ያመሰቃቀለና ሕዝብን ግን በእጅጉ ያስቆጣና ብዙ አገር-ወዳዶችን ከልብ ያሳሰበ ሁኔታ የተከሰተበት በመሆኑ፤ ኢተፖድኅ የሚጠብቀው ትግል ቀላል አለመሆኑ የታወቀ ነበር፡፡ ይኸ  አጠቃላይ ውዥንብርን የፈጠረ ሁኔታም ረጋ ብሎ ማሰብን፣ ብስለትንና አዲስ የኃይል አሠላለፍን የግድ የሚል፣ በሙሉ ኃይል መንቀሳቀስንና የተለየ ትኩረትን የሚጠይቅ ትግል በመሆኑ የአባል ድርጅቶችን የጠበቀ ትሥሥር፣ መተማመን፣ ትኩስ ተሣትፎና ያላሰለሰ ጥረትን እንደሚጠይቅም ግልጥ ነበር፡፡

የፓሪስ-ሁለቱ ጉባዔ ኢተፖድኅን መሥርቶ ሲጠናቀቅ አጠቃላይ ግንዛቤዎቹን፣ የፖለቲካ ድርጅቶች ኅብረትንና የብሔራዊ ውይይት ጥሪን በሚመለከት እና ዴሞክራሲያዊ፣ ነፃና ርትዓዊ ምርጫን በሚመለከት ያለውን አቋምና የሚከተለውን አቅጣጫ ባወጣው የይፋ መገለጫው ላይ አሣውቋል፡፡ (ETEPODEH,_Meglecha.pdf). ኢተፖድኅ በዚኸ መግለጫው "አገራችን ኢትዮጵያ በኤርትራ መወረሯን እያወገዘ፣ ለዚኸ ወረራም የሕወሓት/ኢሕአዴግ ፖሊሲ የማይናቅ አስተዋፅዖ ማድረጉን....፣ ... የወረራው ዓላማ በከፊል በሽራሮና በባድመ የሚወሰን ሣይሆን፣ በመላ ኢትዮጵያ ተዛምቶ ብዙ ግጭቶችን

በማምጣት አገሪቱን ወደ-ባሰ የመከፋፈልና የመተላለቅ ሁኔታ ሊያመራ ስለሚችል....፣ ..የጉዳዩ ባለቤት የሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብና የፖለቲካ ድርጅቶች .... የጋራ መፍትኄ እንዲፈልጉ መንግሥት አመቺ ሁኔታና መድረክ እንዲፈጥር፣.. የኤርትራ መንግሥት በኤርትራ በሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ላይ የሚወስደውን ኢ-ሰብዓዊ እርምጃ በአስቸኳይ እንዲያቆም፣ ... የኢትዮጵያ መንግሥትም ለአገር ደኅንነት በሚል በኤርትራውያን ላይ የሚወስደው እርምጃ የዓለም-አቀፍ ሕግንና የሰብዓዊ መብትን ደንብ ያከበረ እንዲሆን፣.. ነፃና ርቱዓዊ ምርጫን አስመልክቶ ... ከመንግሥት ጋር ለመደራደር ዝግጁ መሆኑን፣ ...” ወዘተ.. በአጠቃላይ ያለውን እምነት በመግለጥና አንዳንድ የውጭ ኃይሎች ለተፈጠረው ጦርነት የሚያሳዩትን አድሎዓዊነት ያለው አመለካከታቸውን እንዲያስተካክሉና ሚዛናዊ አስተያየት እንዲኖራቸው፣ ድርጅቶችም ከኢትዮጵያ ሕዝብና ከሠራዊቱ ጎን እንዲሰለፉ፣ አገዛዙ በሚከተላቸው ሕዝብን ከፋፋይ መርኃ-እቅዶች (ፖሊሲዎች) ሣቢያ በአንዳንድ የአገሪቱ ክፍሎች አሳዛኝ ግጭቶች መከሰታቸው እንዳሳሰበውና በተለይ በጉጂ ኦሮሞና በጌዲኦ መኻከል ከሦስት ሽህ በላይ ለሆኑ ንፁኃን ዜጎች ሕይዎት መጥፋትና ለንብረት መውደም ምክንያት የሆነው ጎሣን መሠረት ያደረገ ግጭት በአስቸኳይ እንዲቆም ጥሪውን በማቅረብ፣ በአገሪቱ ሰላም እንዲሰፍንና ሕዝብ የመብቶቹ ባለቤት እንዲሆን ለሚደረገው ትግል ተጠናክሮ መቀጠል ያለውን ዝግጁነትና ቁርጠኝነት በአፅንዖት ገልጧል፡፡

ኢተፖድኅ ቅድመ-ጉባዔ ተዘጋጅተውና በጉባዔው ላይ ዳብረው የነበሩና ሌሎችንም ወቅታዊ ሰነዶች በማውጣት ሕዝባዊ የጋራ ትግሉ የተሻለ መልክ ይዞ እንዲቀጥል ከፍተኛ ጥረት አድርጓል፡፡ በዚኽም መሠረት የዴሞክራሲና የነፃ ምርጫ አዲስ ትልም፣ የሥርዓት ለውጥና የዴሞክራሲ ሂደት በኢትዮጵያ፣ ሕዝባዊ ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓትና የሕግ የበላይነት፣ ወዘተ.. በሚሉ ርዕሶች ሠፋፊ ሰነዶችን በማውጣት አሰራጭቷል፡፡ ቀደም-ሲል በኢዴኃቅ፣ በፓሪስ-አንድ፣ የአዲስ አበባ የሰላምና እርቅ ጉባዔ፣ በአማራጭ ኃይሎች እንደተደረገው ሁሉ ኢተፖድኅም በአገሪቱ አስተማማኝ ሰላምና መረጋጋት እንዲሰፍንና ሕዝብ መብቶቹ የሚከበሩበት ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እውን እንዲሆኑ ለሚደረገው ሰላማዊ ትግል ያለውን ቁርጠኝነት በመግለፅ ከኢሕአዴግ በኩል በጎ-ፈቃድና ትብብር እንዲኖር ጥያቄውን በደብዳቤ ቢያስተላልፍም፣ የኢሕአዴግ መሪዎች ለቀረበላቸው ጥሪ የሰጡት አንዳችም መልስ አልነበረም፤ በተለመደው የንቀትና ዕብሪት ባኅሪአቸው ዝምታን መርጠዋል፡፡

ኢተፖድኅ ሥራውን እንደ-ጀመረ የውስጥ ችግሮች ብቅ-ብቅ ሲሉ ጊዜ አልወሰዱም፡፡ በአንዳንድ ድርጅቶች በኩል በጉባዔው ላይ የሸዓብያን ወረራ በተመለከተ የተወሰደውን የጋራ ስምምነት በማጣጣልና አልፎም የጋራ ግንዛቤውን እንደሌለ በመቁጠር የዚያ ጦርነት ምንነት ለድርጅቶች መወዛገብ ምክንያት መሆን መታየት ጀመረ፡፡ የኢተፖድኅ መሥራች አባል ድርጅቶችና የኢተፖድኅ አባል ያልነበሩ ኃይሎችን ጨምሮ በዋሽንግተን ዲሲ በተካሄዱ ተከታታይ ስብሰባዎች ላይ ጦርነቱን በተመለከተ ሠፊ ልዩነቶች ተንፀባርቀዋል፡፡ በዚኽም ድርጅቶች ከሁለት የተከፈለ አቋም አንፀባቀዋል፡፡ በአንድ በኩል የኢትዮጵያ ዴሞክራቲክ ኅብረት (ኢዴኅ)፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ ፌዴራል ዴሞክራሲያዊ አንድነት ፓርቲ (ኅብረሕዝብ-ኢትዮጵያ) እና የመላ ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ (መኢሶን) የፓሪስ-ሁለት ጉባዔን (የኢተፖድኅን) የጋራ ግንዛቤና ውሳኔ መሠረት ያደረገ አቋም ሲይዙ ሌሎቹ (ኢሕአፓ፣ ደቡብ ኅብረት፣ አማራጭ ኃይሎች፣ የኢትዮጵያ አንድነትና የዴሞክራሲ ድርጅት (Motherland Party)፣ ሞኣ-አንበሣ፣ ወዘተ... ያንን የተፃረረ አቋም ይዘው ነበር፡፡ ልዩነቱ እየሰፋ በመሄዱም ከሁለቱ የተለያዩ አቋሞች አንዳንድ ሰው (ዶ/ር በዬነ ጴጥሮስ አዲሱን ከኢተፖድኅ ግንዛቤና ውሳኔ ውጭ ያለውን አቋም በመያዝ እና እኔ ደግሞ የድርጅቴን የኅብረሕዝብን፣ የኢዴኅንና የመኢሶንን ተመሣሣይ አቋም በመያዝ ሦስተኛ በጊዜው የኢዴኃቅ ሊቀ-መርንበር ዶ/ር ሙሉጌታ ሥዩም በመሆን በኮሚቴ መልክ ጉዳዩ እንዲታይ ተወስኖ ለማየት ቢሞከረም ልዩነቱን ማጥበብ ባለመቻሉ አዴኅና ኅብረሕዝብ በየራሣቸው ሠፋ ያሉ ይፋዊ የአቋም መግለጫዎችን ማውጣት ተገደዋል፡፡

ኢተፖድኅ በአንድ በኩል የኢትዮጵያ ሠፊ ሕዝብ በትግሉ ቀጥታ ተሣታፊ ብቻ ሣይሆን የትግሉ ማዕከል የሚሆንበትን ሁኔታ በማመቻቸትና ሕዝባዊ ትግሉን በጥንቃቄና በትጋት በመግፋት በፓሪስ-ሁለት ጉባዔ ላይ በፀደቀውና "የዴሞክራሲና የነፃ-ምርጫ ትልም" (Democratization and Free Elections Initiative) በሚል ርዕስ በወጣው ሰነድ ውስጥ የቀረቡት መመዘኛዎችና መሥፈርቶች እንዲሟሉ ጠንካራ እንቅስቃሴ በማድረግ ከገዥው ፓርቲ ከኢሕአዴግ ጋር ምርጫው ነፃና ርቱዓዊ እንዲሆን በመደራደር የምርጫ ውድድር ዘመቻው ሂደት ላይ ተሣታፊ መሆንና ሕዝብን ማደራጀት ያስፈልጋል በሚል እና በሌላ በኩል የለም ሁኔታዎች አስቀድመው ሙሉ-በሙሉ ካልተሟሉ በምንም መንገድ በሂደቱ ተሣታፊ መሆን አያስፈልግም በሚል የፖለቲካ ውሳኔን በሚጠይቅ መሠረታዊ የአሣብና የትግል ትልም ላይ ሠፊ ውይይትና ክርክር ተደርጓል። በጉዳዩ ላይ የነበረው ክርክር የተቋጨው በምርጫው ዘመቻ (በሂደቱ) ተሣታፊ በመሆን እስከ-መጨረሻው ከሕዝብና በሕዝብ መኻል ያለንን ራዕይ የማስጨበጥና በገዥው ፓርቲና በለውጥ-ፈላጊው ዴሞክራት ኃይል መኻል ያለውን የመርኅና የፍልሥፍና ልዩነቶች በግልጥ አሣይቶ ሁኔታዎች በምርጫው ቀን ተሣታፊ ለመሆንና ለሕዝብ ጠቀሜታ የሚሰጥ እውነተኛ ለውጥ ለማስገኘት የማያስችሉ መሆናቸው በጭብጥ ሲታወቅ ከምርጫው ድግስ እራስን ማግለል ይቻላል የሚለውን አሳብ በድምፅ ብልጫ በማሣለፍ ነበር። በዚያ ውሳኔ መሠረትም ኢተፖድኅ በአገር ውስጥ ለሕዝባዊ ትግሉ መሥመር መያዝ ከፍተኛ አስተዋፅዖ ማድረግ የቻሉ እንቅስቃሴዎችን አድርጓል። የሆነ ሆኖ በነበረው አስቸጋሪ የፖለቲካ ሁኔታና በራሱ በኢተፖድኅ ተፈጥሮ (ስብጥር) ምክንያት ድርጅቱ (ኢተፖድኅ) ሊከተለው ያቀደውን የትግል ትልም በተግባር ለመተርጎም ከባድ እንደሚሆን የታወቀ ነበር። ዋናው ችግር አባል ድርጅቶችን በአንድ መሥመር የማቆየትና የትግሉ ትኩረትም የምርጫውን ሂደት ከአንድ ወቅት የምርጫ ክንዋኔ ባለፈ መልክ እንዲጠቅም አድርጎ የማየት፣ የመገንዘብና በዚያም መንፈስ በጋራ ሥነ-ሥርዓትን ጠብቀውና ለጋራ ውሳኔዎች ተገዥ ሆነው እንዲንቀሣቀሱ አለመቻሉ ነበር። በመሆኑም ውሳኔውን ከመጀመሪያ ባልተቀበሉትና በደገፉት አባል ድርጅቶች መኻከል የነበረው ልዩነት ድምፅ ብልጫውን ተከትሎ አላከተመም። ኢተፖድኅ እንኳን ድኅረ-ምርጫ ለሚኖረው ሁኔታ ትግሉ በቀጣይነት እንዲቀጣጠል ሁኔታዎችን ለማመቻቸት ጠንክሮ መሥራት ቀርቶ እስከ ምርጫው ያለውን ጉዞ ጠፈፍ ባለ መልክ መርኁንና ድርጅታዊ አንድነቱን ጠብቆ መጓዝ አልተቻለውም።

በአኳያው የኢሕአዴግ ቁንጮዎች የወጠኗቸውን አፍራሽ፣ ፀረ-ሕዝብና ኢ-ዴሞክራሲያዊ ውጥኖች ተግባራዊ ለማድረግ የሌሎች ትብብር የግድ እንደሚያሻቸው ጠንቅቀው በማወቃቸው ተግተው መሥራት አላቆሙም። ስለሆነም በተናጠል በሚያደርጉት ጉዞ በሕዝብ ዘንድ አመኔታንም ሆነ ተቀባይነትን እንደማያገኙ፤ በውጭ ደጋፊዎቻቸው በኩልም እርዳታና ትብብራቸው እንዳይለያቸው (ቢያንስ ግን እንዳይቀንስባቸው) ለመድብለ-ፓርቲ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እንደቆሙ ሊያረጋግጡ የሚችሉ ሽፋኖች ማግኘቱ አስፈላጊ ሆኖ ስላገኙት፤ ቀደም ሲልም እራሱ ኢሕአዴግ በዚሁና ለዚሁ የተቋቋመ በመሆኑ፤ በልዩ ልዩ ማባበልና ድለላ በተቃዋሚው ጎራ ከተሰለፉት ውስጥ አንዳንድ ግብዞችና ተላሎችን ማስከዳት፣ ያ ሳይሆን ሲቀር በእያንዳንዱ ለእነሱ ትብብሩን በነፈገ ድርጅት ስም አዳዲስ አምሳዮችን በመጠፍጠፍ መንፈሰ-ስንኩሎችንና ጊዚያዊ ጥቅም-አሳዳጆችን "መሪ" እያሉ በመሾም የሚከተሉት የፖለቲካ ይዞታ ሁሉን አሣታፊና "ዴሞክራሲያዊ" እንደሆነ ለማሳየት ጥረታቸውን አላቆሙም። እነዚያ የኢሕአዴግ መሪዎች በፈለጉ ጊዜና እንዳመቻቸው የሚቀያይሯቸው አዲስ ምስለኔዎችም የኢሕአዴግ አውራዎች ብኩን ፍላጎት አሚይና እኩይ ዓላማ አስፈፃሚ በመሆን ከሕወሓት ወደ ኢሕአዴግነት፣ ከኢሕአዴግነት ወደ-ሽግግር መንግሥትነትና በቀጣይም በምርጫ ስም ወደ ቋሚ መንግሥትነት በኢትዮጵያና በሕዝቧ ላይ አምባ-ገነናዊ የአገዛዝ ሥርዓት እንዲያንሰራፉ አገልግሎታቸውን ቀጥ ብለው የሚለግሷቸው ወዶ-ገቦች አጥተው አያውቁም። እንደ እውነቱ ከሆነ ያለ እነዚኽ ወገኖች ቀጥተኛ ትብብርና ምትክ-የለሽ አገልግሎት የኢሕአዴግ መሪዎች እስከ-አሁን በሥልጣን ላይ በያዙት ሁኔታ መቀጠል ጨርሶ የማይታሰብ ጉዳይ ነው።

***በክፍል አሥራ-ሦስት ይቀጥላል.....***